# ምዕራፍ ሁለት

## አብ ማነው?

**ስሙ፡-** ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በባሕርይ በሕልውና በመለኮት አንድ የሚሆን ከሦስቱ አካላት አንደኛው አካል እግዚአብሔር አብ ነው አብም ማለት አባት ማለት ነው። አብ የተለየ አካል አለው። ስለዚህ በተለየ አካሉ ፈናዊ በተለየ ስሙ አብ በተለየ ግብሩ ወላዲ፣ አስራፂ ይባላል። በባሕርያዊ (ኩነታዊ) ስሙ ደግሞ ለባዊ አለባዊ ይባላል። በብሉይ ኪዳንም በሐዲስ ኪዳንም እግዚአብሔር የሚለውን ስም ለአብ ብቻ በመስጠት በእግዚአብሔር አብ ላይ እስከአሁን የተነሣ መናፍቅ የለም ሐልዎተ እግዚአብሔርን ከሚክዱ በቀር።

እግዚአብሔር አብ አብ ይባላል ትርጉሙ ከላይ እንደተመለከትነው አባት ማለት ሲሆን ስምነቱም ስመ አካል (የአካል ስም) ነው። አብ የሚለው ስሙ የራሱ አካል ያለው መሆኑን ይገልጻል ምክንያቱም "አካል ለሌለው አለ ላልተባለ ህልውናው ላልታወቀ ስለሌለ ስም አይሰጠውምና" (ሰዋ. ወግ. መገ ቃ. ኪዳ. ወ. ክፍሌ)

### ሌሎች የግብር ስሞቹም የሚከተሉት ናቸው።

- *ወላዲ፣ አሥራፂ፡-* ይባላል ስሞቹም የግብር ስሞች ናቸው። ቅድመ ዓለም ወልድን ስለወለደ ወላዲ (ማር 1፥11) መንፈስ ቅዱስንም ስለአሠረፀ አስራፂ (ዮሐ 15፥26) ይባላል።
- *ፈናዊ፡-* ይባላል ትርጉሙ ላኪ ማለት ነው። ልጁን ወደዚህ ዓለም ልኮ ዓለምን ስለአዳነ (ዮሐ 3፥16) መንፈስ ቅዱስን በመላክ ዓለምን ስለቀደሰና ስለአጽናና ነው። ዮሐ 14፥12)



- *ለባዊ አለባዊ፡-* ይባላል የሚገነዘብ የሚያስገነዝብ ማለት ነው። ይህ ደግሞ የኩነት ስም ይባላል። በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት አብ በልብ ወልድ በቃል መንፈስ ቅዱስ በሕይወት (እስትንፋስ) ተመስለው ይነገራሉ። (መዝ 44÷1, መዝ 32÷6-7) አብ ለራሱ ለባዊ (አሳቢ ወይም የማሰብ መሠረት) ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ደግሞ (የማሰብ ችሎታቸው) ነው። ወልድ ለራሱ ነባቢ (ተናጋሪ) ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃል፣ መንፈስ ቅዱስም ለራሱ ሕይወት፣ ሕያው ሆኖ ለአብና ለወልድ እስትንፋስ (ሕይወት) ነው። ስለዚህ አብ ከሦስቱ ስመ አካላት አንዱ ነው "አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ" ከሚባሉት። (ማቴ 28÷19, 3÷17) ወላዲ የሚለው ስም ደግሞ ከሦስቱ የግብር ስሞች አንዱ ነው። "ወላዲ አሥራፂ፣ ተወላዲ ሠራፂ" ከሚባሉት። (መዝ 2÷7, 109÷3 ዮሐ 15÷26) ወላዲና አሥራፂ የሚሉት ሁለት ስሞች የሚስማሙት አብን ብቻ ነው፣ ተወላዲ የወልድ ሠራፂ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ የግብር ስሞች ናቸው።

### የወልድ የባሕርይ አባት ነው።

ወልድን ቅድመ ዓለም እንደወለደ ከዚህ በሚከተሉት መጽሐፍ ቅዱሳውያን መረጃዎች መገንዘብ ይቻላል (መዝ 109÷3, ማር1÷11, ዮሐ 1÷18, 3÷16) ሶስት መቶ አሥራ ስምንቱ ሊቃውንት "በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን አንድ የአብ ልጅ በሚሆን" ብለዋል።

*መንፈስ ቅዱስንም አሥርጿል* "ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለእኔ ይመሰክራል" ዮሐ 15÷26 በሚለው ቃል መገንዘብ እንችላለን። ሠለስቱ ምዕትም "ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማኅየዊ ዘሠረጸ እምአብ" ከአብ በሠረጸ አዳኝ ጌታ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስም

እናምናለን ብለዋል። ከዚህ አንጻር መንፈስ ቅዱስ የሚሠርጸው ከአብ ብቻ መሆኑን አርቶዶክሳዊ ልብ ይበልና በእምነቱ ይጽና (ጸሎተ ሃይማኖት ዘኒቅያ)።

## እግዚአብሔር አብ በአካላዊ ቃሉ ዓለምን ሁሉ ፈጥሯል።

መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ቃል ዓለማት እንደተዘጋጁ የሚታየው ዓለም ከማይታየው እግዚአብሔር እንደተፈጠረ ይናገራል (ዕብ 11:1) "በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ጸኑ ሠራዊቶቻቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ" ይላል (መዝ 32፥6) የስድስቱ ቀናት ፍጥረትን እግዚአብሔር አብ በአካላዊ በባሕርያዊ ቃሉ እንደፈጠረ የሥነ ፍጥረት ሁኔታ የተብራራበትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንመልከት።

## እግዚአብሔር የፈጠረውን ሁሉ በቃሉ እንደፈጠረ

### ቅዱስ መጽሐፍ

1. "እግዚአብሔርን ከሰማያት አመስግኑት፣ በአርያም አመስግኑት መላእክቱ ሁሉ አመስግኑት፣ ሠራዊቱ ሁሉ አመስግኑት ፀሐይና ጨረቃ አመስግኑት፣ ከዋክብትና ብርሃን ሁሉ አመስግኑት፣ ሰማየ ሰማያት አመስግኑት የሰማያት በላይም ውኃ እርሱ ብሎአልና ሆኑም፤ እርሱ አዝዞአልና ተፈጠሩም።" መዝ 148፥1-6 ይላል።

ዘማሪው ዳዊት ሥነ ፍጥረታትን ከቈጠረ በኋላ ሁላችሁንም በቃሉ አዝዞ ፈጥሯችኋልና አመስግኑ ያላቸውን ፍጥረታት እንዴት እግዚአብሔር በቃሉ እንደፈጠረ ከማስተማሩም በላይ ለምሥጋና ይጋብዛል።

2. እግዚአብሔር ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ (ዘፍ 1፥3)



3. እግዚአብሔርም በውኆች መካከል ጠፈር ይሁን በውኃና በውኃ መካከልም ይክፈል አለ . . . እንዲሁም ሆነ (ዘፍ 1፥6-7)
4. እግዚአብሔርም፦ ከሰማይ በታች ያለው ውኃ በአንድ ስፍራ ይሰብሰብ የብሱም ይገለጥ አለ፣ እንዲሁም ሆነ . . . እግዚአብሔርም ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል አለ እንዲሁም ሆነ (ዘፍ 1÷9-13)
5. እግዚአብሔርም አለ ውኃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ ወፎችም ከምድር በላይ ከሰማይ ጠፈር በታች ይብረሩ (ዘፍ 1÷20-23)
6. እግዚአብሔርም አለ ምድር ሕያዋን ፍጥረታትን እንደወገኑ እንስሳትንና ተንቀሳቃሾችን የምድር አራዊትንም እንደወገኑ ታውጣ እንዲሁም ሆነ . . . እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር. . . እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ (ዘፍ 1÷24-28) በእነዚህ የስድስት ቀናት ፍጥረታት ሥርዓተ ተፈጥሮ ላይ እንደተገለጸልን እግዚአብሔር ይሁን በማለት በባሕርያዊ ቃሉ ዓለምን እንደፈጠረ ልብ እንበል።

## አብን የሚያውቀው ማነው?

### 1. አብን በባሕርይ አውቅና የሚያውቀው ወልድ ነው፤

". . .ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቀው የለም ከወልድም በቀር ወልድም ሊገልጥለት ከሚፈቅድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም" (ማቴ 11÷27) ይላል የእግዚአብሔር ቃል። በዚህ መሠረት የሕልውና እውቀት አብን የሚያውቅ ልጁ ኢየሱስ ነው።

### 2. መንፈስ ቅዱስ፤

". . . መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው።

በእርሱ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቀውም።" (1ቆሮ 2፥10-12) በዚህ ቃለ እግዚአብሔር መሠረት ባህርያዊ ሕይወት መንፈስ ቅዱስም አብን ባሕርያዊ በሆነ ዕውቀት ያውቀዋል።

*ማሳሰቢያ፦* አንድ ሰው ሌላውን የሚያውቀው አይነት ዕውቀት አይደለም። ሦስቱ አካላት በአንድ መለኮት ያላቸውን ዕሪና የሚገልጽ ጥቅስ ነው እንጂ።

### 3. *ኢየሱስ ክርስቶስ የገለጠለት ያውቀዋል፤*

"ወልድ ሊገልጥለት ከሚፈቅድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም።" (ማቴ11፥27) እንደተባለ። እንዲሁም በወልድ የሚያምን አብን ሊያውቀው ይችላል። ". . . አባትህ ወዴት ነው? አሉት ኢየሱስ መልሶ እኔንም ወይንም አባቴንም አታውቁም እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁት ነበር አላቸው።" (ዮሐ 8፥19) በሌላ መልኩ ደግሞ ልጁ ስለ አባቱ የተረከውን የሚሠማ ሊያውቀው ይችላል። "መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።" እንዳለ ቅዱስ ዮሐንስ (ዮሐ 1፥18) ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎች በእርሱ በኩል ብቻ ወደ አብ እንደሚደርሱ ተናገረ (ዮሐ 6፥46, ዮሐ 14፥6-11) ስለዚህ ማናቸውም ክርስቲያን አብን ለማወቅ ወደ አብ ለመቅረብ ወደማያውቀው የምሥጢር ከተማ ለመድረስ በልጅነት መንፈስ መቀደስ በጽድቅና በሕይወት መንገድ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል መጓዝ ይገባዋል። የበጎች በር እርሱ ነውና በእርሱ በኩል መግባት ይገባዋል። (ዮሐ 10፥7)